2019/04/24

# የአንዳርጋቸው ጽጌ ስብሰባ ያለስምምነት ተጠናቀቀ።

ዛሬ ሚያዚያ 16/2011 ዓ.ም ወረታ ካምፕ የነበረው የአንዳርጋቸው ጽጌ ስብሰባ ያለስምምነት ተጠናቋል።አንዳርጋቸው ጽጌ ሰራዊቱን በ600 መቶ ብር ለመደለል ሞክሮ ነበር። ግን አልሆ ነም። ሰራዊቱ የጉባኤ ተወካይ አንልክም በማለት በአቋሙ ጸንቷል።የሰራዊቱ ምክንያትም፡-

፩ኛ ኤርትራ በርሃ ላይ በመዳበሪያ ተቋጥሮ ዱቄት ቤት የተጣለው አጽም ሳይመጣ፣ እኛ በጉባኤ አንሳተፍም ብሏል

፪ኛ እኛ ሳንቋቋም በጉባኤው አንሳትፍም ብሏል።

፫ ሰራዊቱ በላቡ የገዛቸው ንብረቶች ለሰራዊቱ ሳይመለሱ፣ግንቦት 7 በካዝናው ይዞ እኛ ጉባኤ አንሳተፍም ብሏል።

፬ኛ ሰራዊቱ አማራ ጠል በሆነ ድርጅት በሚያዘጋጀው ጉባኤ ላይ እኛ አንሳተፍም ብሏል ።

እናም አንዳርጋቸው ጽጌ ጠጉሩን እየነጨ በመጣበት እግሩ ተመልሷል።ከውጭ ለመጣው ሰራዊት ለእያዳንዱ 600 ብር በመስጠት ለመደለል ቢሞክርም ሴራው አልተሰካለትም።

ሰራዊቱ ባህርዳር ላይ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ቀነ ቀጠሮ ቆርጧል።እንግዲህ እኛም እንሰለፋለን።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ "እናተ በጉባኤው ባትሳተፉም ድርጅቱ ጉባኤ ያደርጋል" ሲል በአጭበርባሪ ምላሱ ገልጾ ወደ መጣበት ተመልሷል።ሰራዊቱም "ሚዚያ 29/2011 ዓ.ም የሚደረገውን ጉባኤ በእኛ ዘንድ እውቅና የለውም ብሏል።"

ክብር ለቁርጥ ቀን ጓዶቼ።ሁሉም አማራ ከጓዶቼ ጎን ይሰለፍ ዘንድ በዚሁ አጋጣሚ አበክሬ እገልጻለሁ።

በመጨረሻም በስብሰባው ፎቶ እንዳይነሳ፣ቪዲዮ እንዳ ይቀዳ አቶ አንዳርጋቸው በልዩ ሃይል አስከልክሏል።